Solidarity Movement for a New Ethiopia

# ግልፅ ደብዳቤ ለፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ, በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ስለአለው የሰላምና መረጋጋት አሳሳቢነት፤



ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

የተከበሩ ባራክ ኦባማ የአሜሪካ ፕሬዚደንት
ዋይት ሀውስ
1600 ፐኒስይሊባንያ ጎዳና
ዋሽንግተን ዲሲ 20501

ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን

ይህን ደብዳቤ የምጽፍልዎ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄን /አኢትን/ በመወከል ሲሆን የንቅናቄው መሠረታዊ ተልኮም በህዝቡ የእለት ተእለት ሕይወት ውስጥ የማህበራዊ ፍትህ እንዲኖር፣ በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሚገኙባቸው አካባቢአቸው፣በብሄረሰብ፣ በፓለቲካና በሀይማኖት በተደራጁባቸ ዘርፎች ሁሉ በመተባበር በአሁኑ ወቅት የጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ አምባገነን አገዛዝ ያሰፈነውን ጭቆናና የሰብአዊ መብት ጥሰት ብሎም የፍትህ እጦት በጋራ እንዲታገሉ ማስተባበር እንደዚሁም ግልጽነት ነፃነትና ማህበራዊ እርቀ ሰላም በኢትዮጵያ እንዲሰፍን የማድረግ ተልእኮ ይዞ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው።

ዋና አላማችን “ሰብአዊነትን ከብሄረሰብ በፊት ማስቀደም” የሚል ሲሆን በሌላ አባባልም ለሁሉም የሰው ዘር እኩል ክብር መስጠትና ሁሉን አቀፍ ለሆኑት ነፃነትና ፍትህ ብሎም ለሰብአዊ መብት መከበር እንዲቆሙ ለማስቻል “ሁላችንም ነፃ ካልወጣን ማንም ነፃ ሊወጣ አይችልም” የሚሉ መሰረታዊ መርሆዎችን እናራምዳለን።

በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ እየከፋ የመጣው የሰላም እጦትና ውጥረት በቸልታ የሚታለፍ ወይም "በር ዘግቶ" አለያም በሚስጥራዊ ዲፕሎማሲ የሚፈታ ችግር አይደለም። ይህ አይነት ዲፕሎማሲ ሂደት ጭራሹኑ በአፍሪካ ከታወቁት አንዱ ለሆነው የኢትዮጵያ ጨካኝና አምባገነናዊ አገዛዝ ሽፋን ሰጭ አሰራር ነው። ይህ አገዛዝ በስልጣን ላይ ሆኖ በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ እያሰቃዬ ባለበት ሁኔታ ሰላምና መረጋጋት በአፍሪካ ቀንድ ማሰብ ስህተት ነው።

መለስ "የአፍሪካ ጠንካራው ሰው "ቢያንስ ከሱዳኑ ኦማር አልበሽር እና ከዚምባብዌ ሮበርት ሙጋቤ ጋር እኩል ሊመዘኑ ይገባል፡ ለእንዲህ አይነቱ አምባገነን መሪ የተሻለ ይዞታ መስጠት ሌሎችን ተመሳሳይ ስራ የሚሰሩትን ማውገዝ እርስ በእርሱ የሚቃረን መርህን ያልተከተለ አሰራር ነው። ይህ ሂደት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ጥላቻ የሚያተርፍ ያለፈው የቡሽ አስተዳደር የፈጸመውን ስህተት መድገም ነው።

የአባቶቻችን ምኞት የነበረው "አፍሪካን በሰላምና በፍቅር ወደ ተሻለ ተስፋ ማምራት ነበር"። ያለ መታደል ሆኖ በአሜሪካና ምዕራባውያን የውጭ መርህ የተነሳ ይህንን ጨቋኝ መንግስት ከማውገዝና ከማጋለጥ ይልቅ መጠነ ሰፊ የሆነ የገንዘብ ስጦታና ወታደራዊ እርዳታ በመለገስ እውነተኛውን ገጽታ በመሸፈን የቀደምቶቻችን ተስፋ እንዲመክን እየተደረገ ነው፡።

ፕሬዚደንት ኦባማ የእርስዎ አስተዳደር የእኛን ሥራ እንዲሰራ አንጠይቅም ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያደርገውን ዴሞክራሲያዊ ትግል ምዕራባውያን ነፃ ሀገራት መሠናክል አትሁኑን ነው የምንለው። የተከበሩ ፕሬዘዳንት አሁን ከሁለት ነገሮች አንዱን መምረጥ አለበዎት፡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆም ወይም "የአሜሪካ የፀረ ሽብር ጦርነት አጋር ከሆነውና የኢትዮጵያን ችግር እያመሰውና እጅግ በጣም ሰር እየሰደደ እንዲመጣ እያደረገ ካለው አገዛዝ ጋር መሠለፍ" በዚህ መንግሥት አገዛዝ መጥፎነት የተነሳ ብዙው ኢትዮጵያዊ ፊቱንን በእሱና እና በደጋፊዎቹ ላይ እንዲያዞር እየተገደደ ነው። ይህም በአካባቢው የረዥሙን የአሜሪካን ጥቅም የሚነካ ችግር እየሆነ መምጣቱ የማይታበል ጉዳይ ነው።

በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አገዛዝ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሂደት እየተጎዳ መሆኑን፣ በሰብአዊ መብት ላይ ስለሚፈፀም ጥቅል ግፍ፣ የፍትህ ፓለቲካዊ ባህሪ መያዝ፣ ሕዝብ ሽብር ላይ መሆኑን በመረዳት አስተዳደረዎ በግልፅና በማያሻማ መልኩ መለስ ዜናዊን አምባገነን ነወት ብሎ ሊጠራቸው ይችላልን? ከዚህም በላይ የጅምላ ጭፍጨፋና በሰብአዊ ፍጡር ላይ የተፈፀመውን ድርጊት በማጣራት ወደ አለምአቀፍ የወንጀል መከላከሉ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ በሚደረገው የምርመራ ሂደት ይተባበራልን?

በቀጣዩ አምስት ወራት ውስጥ ሀገር አቀፍ ምርጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ይደረጋል።ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድንቅ ለውጥ የሚያሳዩበትና ድጋፍ የሚሰጡበት ጊዜ አሁን ነው። ይህ ተጨባጭ እርምጃ በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ያለውን ቀውስ ለማስቀረት ብሎም በአለም በግጭት ከታወከው አካባቢ አንዱ የሆነውን ይህን ክልል የዴሞክራሲ ሂደት መጠናከር ተጨማሪ እርምጃ የሚጠይቅበት ጊዜ ይህ ነው። ነፃዋ ኢትዮጵያ እርስ በእርሱ በተሳሳረው አካባቢ ሰላም በማምጣይ ጉልህ የሆነ ድርሻ አላት።አሁን ያለው ጨካኝና አምባገነን መንግሥት በአካባቢው የፈጠረው ነገር ቢኖር መከፋፈል፣ ግጭት፣ አመፅና የወደፊት የሽብርተኞችን ባህሪ ይበልጥ እንዲከር እያደረገ መምጣቱ ነው።

እስከ አሁን አስተዳደረዎ በኢትዮጵያ ላይ የሚከተላቸው መርሆዎች ከቀደምቱ የቡሽ አስተደደር ጋር ተመሳሳይ ናቸው። የኢትዮጵያን ሕዝብ የዲሞክራሲያዊ ንቅናቅቄ ድጋፍ ነፍገዋል፤ ወይም የዲሞክራሲያዊ ተቋማትን ለመገባት በምሥራቅ አውሮፓ እንደ ዩጎዝላቪያና ሎሎች አካባቢዎች የተወሰደ አይነት እገዛ አልተደረገም በዋሽንግተን ዲሲ ለዴሞራሲያዊ ሂደትን ለማጠናከር የሚሰጠውው ገንዘብ፤ በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በሌሎች ተቋማት ለዲሞክራሲ ግንባታ የሚደረጉት እገዛዎች አልያም ኢትዮጵያን አልፈዋታል ወይም

በትክክለኛ ለዲሞክራሲ ግንባታ የሚታገሉትን ትተው መለስ ዜናዊ ለሚቆጣጠሯቸው ተቋማት ይሰጣሉ ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ምራባዊያን ሌላ አማራጭ የለንም በሚል ለአምባገነኑ መንግሥት ድጋፍ መስጠታቸውን እውነተኝነት ሲነግሩን ይደመጣሉ። በዚህ ረገድ ሌላ አማራጭ የሚሆኑ ወገኖችን መለስ እያጠፋቸው ይገኛል። ምዕራባዊያን  እንኳንስ አማራጭ ሀይሉን በመደገፍ ለማሳደግ መሞከር ይቅርና ቢያንስ አገዛዙ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚፈጽመውን ደባ ለማውገዝ እንኳ ፈቃደኛ አይደሉም።

ክቡር ፕሬዚደንት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ጉዞ አስመልክቶ አስተዳደረዎ በጣም የፈዘዘ ሂደትን በመከተሉ የተነሳ ይህን ደብዳቤ ለመፃፍ ተገደናል። እርሰዎ የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም መጠበቅ እንዳለበወት ይገባናል። በዚህ ረገድ የሌላውን ነፃነት በመጫን፣ሐብቱንና እለታዊ ኑሮውን በማዛባት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሳሆን የሁለቱን ሀገራት ጥቅም ያቻቻለ ግንኙነት ላይ መመስረት አይቻልምን? እርስዎ የአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም ለመጠበቅ እንደሚያደርጉት ሁሉ እኛም የኢትዮጵያዊያን የመጭ እድል እንዲጠበቅ እንፈልጋለን፡ ይህ ከሆን ታዲያ በሁለታችን መካከል የጋራ ጥቅምን የጠበቀ ግንኙነት ለማድረግ አይቻልምን?

አሜሪካ ሕወሓትን የምትደግፈው የአፍሪካ ወታደራዊ እዟን በኢትዮጵያ በመመስረቷ ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ማወቅ ይፈልጋል። አስተዳደረወት ይህን በድብቅ ፈጽሞ ከሆነና በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ ህዝብ ስቃይ ላይ ከወደቀ የተሰራው ተግባር ድቡሽት ላይ የተመሠረት ቤት መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የአገሩን ህዝብ እያሸበረ ባለበት ሁኔታ የእርሰዎ መንግሥት ድጋፍ የሚያደርገው  የሽብርተኞችን እንዲያጠፋ ታልሞ ከሆነ የሚከተሉት መርህ ፈጽሞ የተሳሳተ መሆኑን በአክብሮት ልንገልጽ እንወዳለን። ሂደቱም ውሎ አድሮ አደጋ ያለበት መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ከእንደዚህ አይነት መርህ ይልቅ በእኛ እምነት በምሥራቅ አፍሪካም ሆነ በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን ሕዝቡን በትግሉ ሊያሳትፉ የሚችሉበትን አሰራር ቢከተሉ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ማስገንዘብ እንፈልጋለን፣ የሽብርተኞችን መስፋፋት በአካባቢው የማስቆም ትግል የሚካሄደው በእኛ ቦታ ላይ ስለሆነ የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶችም እኛ ነን፣ በመሆናችን ችግሩ ከማንም በበለጠ የሚያሳስበን  መሆኑም በሰፊው ሊታወቅ ይገባል።

እንደ መለስ ዜናዊን የመሰለ አገዛዝ ለአሜሪካም ሆነ ለምዕራቡ አለም  ሰላምን ያመጣል ብላችሁ ትረዳላችሁ?  በኦጋዴን ወይም በሱማሊያ  ወደ 20 ሺህ የሚገመቱ ሰላማዊ ነዋሪዎች መገደላቸው፣ በከፍተኛ ደረጃ የተሰራጨው ቸነፈር፣ የህዝቡ መፈናቀል፣ የቤታቸውና ምርት መጋየት፣ እየከፋ ያለው የሴቶች መደፈር፣ የእንስሳት መገደል መኖሪያቸው በመርዝ መደብደቡ ስልት ሽብርተኞች ይበልጥ መሰረት እንዲጥሉ እያደረገ አይደለምን? ሶማሊያ ወይም ምሥራቅ ኦጋዴን አሁን በተያዘ ስልት ሽብርተኞችን አጽድቷልን?

ይህ የመሰለ የመለስ ዜናው ሥራ ለማናችንም እንዴት የተሻለ ሂደት ለወደፊቱ ሊፈጥር ይችላል? ይህ ሁኔታ አሜሪካ ቢፈጠር ኑሮ የቢስማርክን ገበሬዎች፣ ዳኮታን መምህራን፣ የዳህላስ ነጋዴዎችን፣ የኔቫራስካ ሳይንቲስቶችን ሀሳብ ያናውጣል አልፎ ተርፎ የኦሬጋን እናቶችን ቤት እንዲውሉ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ የብዙሀኑን አሜሪካን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ አይደለም። በመጨረሻ ውጤቱም  ፀረ- ምእራብ ስሜት እንዲጎለምስ የሚያደርግ ነው። በመጨረሻ አሁን ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን እውነታውን የሚያውቁትም ጥቂቶች ናቸው ምክንያቱም ጋዜጦች ተዘግተዋል ብዙወቹ ፀጥ እንዲሉ ተደርገዋል። የእርስዎ አስተዳደር ሁላችንም የምናምንበትን ለውጥ ሊያደርግ ለምን አልቻለም?

የአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች ለእርስዎና ለአስተዳደረዎ እጃቸውን ዘርግተው እየተጠባበቁ ነው፣ እርስዎ የሚጠብቁዎትን እጆች ሊያስተባብሯቸው ይችላሉ? አስተዳደርዎ በቀንዱና በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የሚፈልጉ ከሆነ ትብብሩን መፍጠር ያለበት ከሕዝቡ ጋር መሆን ይኖርበታል።

አሁን ይህን የምንገልጸው ኢትዮ_አሜሪካዊ በመሆናችን ነው። ይህም ተመሳሳይ የሰው ልጅ ክብር፣ ነፃነት፣ ዴሞክራሲ እና የሕግ የበላይነት በኢትዮጵያም መኖር አለበት። ይህን በማጣታችን ነው ብዙወቻችን ወደ አሜሪካና ቀሪው ምእራብ ሀገራት የመጣነው። ሰላም፣ ደህንነት የኑሮ ዋስትና በኢትዮጵያ እንዲኖር እንፈልጋለን በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ሽብርተኝነት የሚያከትምበት መንገድ አብረን መፍትሄ መፈለጉን እንሻለን፡ ብዙዎቻችን ችግሩ በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲፈለግ እንፈልጋለን፣ ይህም በጥይት ሳይሆን በድምጽ አሰጣጥ ዘዴ እንዲፈታ ምኞታችን ቢሆንም ጥረታችን ግን አሻጥር ተፈጸመበት።

በግንቦት 1997 ዓ.ም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን "የሚያምኑበትን ለውጥ እውን ለማድረግ" በአዲስ አበባ አደባባይ ወጡ። ይህም በአፍሪካ ከተካሄዱት ሰልፎች ሁሉ በሰላማዊነቱ ቀዳሚነት ያለው ነበር።በዚሁ ሰልፍ አንድም ጠጠር አልተወረወረም፤ መስታዊት አልተሰበረም፤ ምርጫው በተካሄደበት እለት 26 ሚሊዮን ሕዝብ ለድምጽ መስጠት ወጥቶ ነበር ። የምርጫው ውጤት ግን በመለስ ተሰረቀ ። መራጩ እግዜብሄር የለገሰውን መሰረታዊ መብት ለማስጠበቅ የምርጫው ውጤት እንዲከበር ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ሲጠይቅ የመለስ የፀጥታ ሰዎች 193 ሰላማዊ ሰልፈኞችን ገደሉ። ከ50ሽህ በላይ አሰሩ፣ አጋዙ፣ በማከታተልም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ለእስር ዳረጉ። ይህ ሁሉ ሲፈጽም አሜሪካ በሚገባ ታውቃለች፣ የቀድሞው አስተዳደርም ይህንን በተመለከተ መግለጫ ከመስጠት ተቆጠበ፣ ሳያወግዝም ቀረ፣ ይህ አቋም የመለስን መንግስት መደገፍ፣ እውቅና መስጠት አይነት ባህሪ ያዘ ብሎም ያልተመረጡት መለስ ዜናዊና ፓርቲያቸው ሕወሓትን ማጠናከርና የህጋዊነት ገጽታ ሽፋን ያለው አስመሰለው።

በአሁኑ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲ ከፍተኛ የሆነ የብዙሀን ድጋፍ ያለውና የመጀመሪያዋ የሴት መሪ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ የህሊና እስረኛ ነች። ሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችም ይዋከባሉ፣ የመገናኛ ብዙሀን ከመንግሥት ውጭ ለሌላው ሁሉ በራቸው ተከርችሟል። እስከ አሁን መጭው ምርጫ ነጻና አግባብ ያለው ይሆናል የሚል እምነት አልተጣለበትም። በቀጣዬ አምስት አመት በዚህ መንግስት ኢትዮጵያ መገዛቷ ከቀጠለ አሁን እየተብላላ ያለው ንዴትና ብሶት ገንፍሎ አመፅ ሊለኩስ ይችላል የሚል ብርቱ ስጋት ደቅኗል። ይህም አመፅ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ወደ ቀሪውም የቀንዱን ሀገራት ሊዛመት ይችላል።

ለመሆኑ የኦባማ አስተዳደር ሌሎችም ምእራባዊያን ሀገራት የኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ይደግፋሉ? በእውነት ለመናገር በእኛ በኩል ግን ተስፋችንና ምኞታችን መንምኗል። ታሪክ እንደሚያስረዳው በዚህ ዓለም ወስጥ የሚገኙት ኃያላኑ ሀገራት በአፍሪካ በተደጋጋሚ በደል አድርሰዋል። ከአህጉሩ አምባገነን መሪዎች ጋር በማበርና የሕዝቡን መብት በመንፈግ ወይንም የወደፊቱን የአፍሪካ እድል በማጨለም በአፍሪካ ሀብት ምጣኔ ሀብታቸውን አበለጸጉ። አፍሪካን ጨምሮ ሁሉም ፍጡር እግዜብሄር የለገሰው ሙሉ ሰብእና አለው በሚል እምነት ባለፈው የፀረ ባርነት ትግል የተሰለፉ ጥቂቶች እንደነበሩ እያስታወስን አሁንስ ገጽታውን ለውጦ የመጣውን ችግር በተመለከተ? እነዚህ የዘመናችን የሞራላ ጥያቄዎች ናቸው።አሁን በከፍተኛ ደረጃ የምንነጋገረው የወቅቱን እውነተኛውን የፖለቲካ እርምጃ ከሆነ አሁንም ደካማው በሀያላን እየተበደለ ነው። ምክንያቱም በምጣኔ ሀብትና በወታደራዊ ኃይል ብርቱዎች ስለሆኑ ከዚህ እርምጃ መውጣት አልተቻለም፡ ታሪክ ግን ወደፊት ይመዝነናል። የሌሎችን ሀገራት ትተን ኢትዮጵያን ብንመለከት ይህ ቀደም ብሎም ተፈጽሟል።

*በ1928 ዓ.ም የኢትዮጵያው ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የወቅቱ የአለም መንግስታት ማህበርን የኢጣሊያኑ ሞሶሎኒ በኢትዮጵያ ላይ በተለይም በደቡባዊ ምስራቅ ግዛት የሚያደርገውን የጦርነት ወንጀል እንዲያስቆሙ ጠየቁ፣ የተፈለገው ትብብር ግን አልተገኘም። እንደውነቱ ከሆን ሁለቱም ሀገራት የማህበሩ እኩል አባላት ነበሩ የሊጉ ሀገር ጥቃት ሲደርስበት ተባብሮ መከላከል መሰረታዊ ደንቡ የደነገገው ነበር። ማህበሩ ግን የሊጉን ደንብ ከማስከበር ይልቅ የወቅቱን ኃያላን ጥቅም ማስቀደም ቅድሚያ ሰጠው።*

*በዚሁ መሰረት የሊጉ ኃያላን ሀገራት ስጋታቸው የኢጣሊያኑ አምባገነን በፀረ-ሂትለር አቋሙ እንዲቆይላቸው ስለነበር ኢትዮጵያን መስዋእት አደረጉ። ለንጉሰ ነገስቱ የሰጡት ምላሽ በጣም የይስሙላ ነበር። ይህ የአባል ሀገርን መብት አለማስከበር እርምጃ ሳይውል ሳይነጋ የድርጅቱ ዋና ፈተና ሆነ፡። ይህም እርምጃ በተቃራኒው ሂትለር እንዲጠናከር አስቻለው፡ በዘመኑ አለም አቀፉ ህብረተሰብ የፖለቲካ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲሉ ኢትዮጵያን ማግለሉን አስመልክቶ ታየምስ መጽሄት በሀምሌ 14 ቀን 1928 ዓ.ም ባወጣው እትሙ እነሱ ይህን ቢያደርጉም ብዙ አፍሪካ አሜሪካዊያን ሙሶሎኒን በመውጋት ከኢትዮጵያ ጎን መሰለፋቸውን ጽፎ ነበር በአሜሪካ የሚሸጠውን የጣሊያን ጅን መጠጥ ሳይቀር ማእቀብ ጣሉበት። ”ከኢጣሊያን ገዝተን አንድ ጊዜ የምንጎነጨው ጅን ሙሶሎኒ የአፍሪካን ወንድሞቻችን መግደያ ጥይት መግዣይጠቀምበታል” በሚል እቀባውን አጠናከሩ የሊጉ ወሳኝ ሀገራት ግን በጋራ ከተስማሙበት ደንብ ይልቅ የየሀገራቸው ብሄራዊ ጥቅም አስቀደሙ፣ በመጨረሻም በጣሊያን ላይ ጥለውት የነበረውን ደካማ ማእቀብ ተብዬ ሳይቀር አነሱ።*

*ለዚህም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የሰጡት ምላሽ እንዲህ የሚል ነበር።”እኔ ፈጣሪ እራሱ እንደኔ ህዝብ በሰቃይ ላይ ያሉ መንግሥታት እንዲጠብቃቸው እጸልያለሁ፤ አለም አቀፉ ሞራል፣ ሰብእና አደጋ ተደቀነበት፣ ኃይለኛ  የሆነው መንግሥት ምንም በደል የሌለበትን የሌላውን መንግሥት ህዝብ ለማጥፋት የሚገባው መስሎት በተነሳ ጊዜ ተጠቂውን ወገን ለመንግስታቱ ማህበር የተበደለውን የሚያቀርቡበት ስዓት ነው። እግዜብሄርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ። የተባበሩት ኃይሎች እስከሚንቀሳቀሱ ድረስ እጠብቃለሁ ካልመጡ ግን ጉዳዬ በእነርሱ በመረረ መልኩ ምእራባዊያን እንደሚደርስባቸው” ገልጸው ነበር።*

*የተከበሩ ፕሬዚዳንት “የአሁኑ አስጊና አስቸኳይ ሁኔታ “የሞራል ውድቀት ነው ይኸውም የአሜሪካን ማንነት በአሁኑ አመት ብቻ ሳይሆን ለመጭውም የሚፈታተን ነው። ታዲያ አሁንም ኢትዮጵያ የዚህ አይነት የአሜሪካ ማንነት መግለጫ ባህሪ እየሆነች ነው። እውን አሜሪካ እና ምእራባዊያን የተመሰረቱበትን መሰረታዊ ባህሪይ ይከተላሉ? ወይንስ ምእራባዊያኑም ሆኑ አሜሪካ የሞራል ባህሪያቸውን ቀይረው በአዲሱ የሽብርተኝነት ትግል ትኩረታቸውን በመጣል ጠቅላላውን አለም የነበረቸውን ጠንካራ የሰብአዊነት ክብር ይጥሉታል? ደካማ ውግዘት የሞራል ጥንካሬን ያኮስሳል ይህም የአለምን ደህንነት ሞጭጮ የመያዙን መሰረታዊ ገጽታ ይለውጠዋል።*

*ኢትዮጵያ በ1928 ዓ.ም ሊጉ ሲያገላት የሚያስከትለውን ሁኔታ በወቅቱ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር። ነገር ግን ውሎ ሳያደር የአለምን ደህንነት ሊከላከል የሚገባውን ጠንካራ ወገን ኃይል አዳክሞ የተከተለው ጭፍጨፋ የታሪክ ምስክር ነው።እንግዲህ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን መቆም ወይም አምባገነን መደገፍ አስተዳደረወና ምእራቡ አሰላለፉን መምረጥ አለበት።አሁን ያለው ችግር ከተጠበቀው በላይ ሊዘልቅ እንደሚችል መገመት ተገቢ ይሆናል።*

እኛ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ጥቅም በመተማመን እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ እውነተኛ ግንኙነት እንዲገነባ የአስተዳደረወትን ምላሽ በጉጉት እንጠብቃለን፤

አክባሪዎ

ኦባንግ ሜቶ
የአዲሲቱ ኢትዮጵያ ትብብር ንቅናቄ ሥራ አስፈጻሚ
ፖስታ ሳጥን ቁጥር 50561
ኦርሊግቶን ቪኤ 22205
ስልክ 202-725 1616
Email obang@solidaritymovement.org
www.solidaritymovement.org

ግልባጭ
_ለክቡር ጆሴ ባይደን ም/ፕሬዚዳንት
_ለክብርት ሂለሪ ክሊተን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
- ለክቡር ሮቨርት ጌት መከላከያ ሚኒስትር
_ለክቡር ጀ/ል ጀምስ ጆንስ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ
_ለክቡር ጆን ኬሪ የውጭ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ኃላፊ
- ለክቡር ሪቻርድ ጂ.ሉገር የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል
-ለክቡር ዶናልድ ቤይን የተወካዮች ምክር ቤት የአፍሪካ ጉዳይ ኃላፊ